ብጹእ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለሐዋርያዊ አገልግሎት ላስ ቬጋስ ከተማ ገቡ።

++++++++++++++++++++++++

#CaNvAz Diocese | ሰኔ ፲፩ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም U.S.A

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በነገው ዕለት በላስ ቬጋስ ከተማ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ለሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል ዓመታዊ ንግሥ በዓል ላይ ለመገኘት ፣ በከተማው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ለመባረክ እንዲሁም ምዕመናንን ለማስተማር ዛሬ ከሰዓት ላስ ቬጋስ Harry Reid ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሰዋል። መልአከ ሥብሃት ቆሞስ አባ ኃይለ ኢየሱስ የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የደብሩ አስተዳዳሪ ከደብሩ ካህናት ጋር በመኾን በ Harry Reid ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በመገኘት አቀባበል አድርገውላቸዋል። በተመሳሳይ በማለዳ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ዶ/ር የኒውዮርክ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ በዓሉን ለማክበር ላስ ቬጋስ ደብረ ምሕረት ቅ/ሚካኤል ደብር ደርሰዋል። ተጨማሪ ምሥል እንደደረስን የምንለቅ ይኾናል።